ከመ/በ/ቶ 1.0/79/6

01 ታሕሳስ 2003

The Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>ባያሉበት</u>

## ጉዳዩ:- መመሪያ ስለመላክ፤

ለመረጃ አቅራቢዎች ሽልማት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 49/2003 እና ሕገወጥ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ላይ ስለሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 50/2003 ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ለኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ እና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለለውጥ ትግበራና ደጋፊ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ለአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ለምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
ለምሥራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዳማ</u>

ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>ባህርዳር</u>

ለጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>ጅጅጋ</u>

ለድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>ድሬዳዋ</u>

ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>መቀሌ</u>

ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>ኮምቦልቻ</u>

# በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94

# መሰረት ለተጨባጭ መረጃ አቅራቢ

# ስለሚሰጥ ሽልማት የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 49/2003

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ኅዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ለተጨባጭ መረጃ አቅራቢ ስለሚሰጥ ሽልማት የወጣ

# መመሪያ ቁጥር 49/2003

መግቢያ

በሀገሪቷ በየወቅቱ እያደገ ከመጣው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የግብር ከፋዮች ቁጥር መጨመሩ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞም ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ትክክለኛ ገቢያቸውን አስታውቀው ግብር የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች የመኖራቸውን ያህል በተቃራኒው ግብር የመክፈል ግዴታን ላለመወጣት የሚደረግ ጥረት መኖሩ የታወቀ በመሆኑ፤

ግብር ላለመክፈል እና ግዴታን ላለመወጣት የሚደረግ ጥረትን የባለሥልጣን መ/ቤቱ ብቻውን በሚያደረገው ክትትል መቆጣጠር አዳጋች በመሆኑ ድርጊቱ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ የግብር ስወራን እና ማጭበርበርን በመከላከል የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ ትክክለኛውን ግብር በሚገባ ለመሰብሰብ ይችል ዘንድ፤

ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በሚደብቅ፣ አሳንሶ በሚያስታውቅ፣ በሚያጭበረብር ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ግብር በማይከፍል ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርተው ጥቆማ የሚያቀርቡ ሰዎችን ለማበረታታት እንዲቻል የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 84/3/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለተጨባጭ መረጃ አቅራቢ ስለሚሰጥ ሽልማት የወጣ መመሪያ ቁጥር 49/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚከተሉት ቃላት እና ሀረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

1. "አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ነው።
2. "ሌሎች የታክስ ህጎች" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94፣ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95፣የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/90 ወይም የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 ናቸው።
3. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለስልጣኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል።
4. "ግብር" ማለት በአዋጅ ቁጥር 286/94 መሠረት የሚከፈል የገቢ ግብር ነው።
5. "ተጨባጭ መረጃ" ማለት ግብር የሚከፈልበት ገቢ መደበቁን፣በማሳነስ ማስታወቂያ መቅረቡን፣መጭበርበሩን ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ግብር አለመከፈሉን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ የሚያቀርበው እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(1) የተመለከቱትን ሁኔታዎች አካቶ የያዘ መረጃ ነው።
6. "ሠራተኛ" ማለት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 155/2000 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።
7. "ተሿሚ" ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ዐቃቢያነ ህግ ናቸው።
8. "መረጃ አቅራቢ" ማለት መረጃ ለባለሥልጣኑ የሚያቀርብ ሰው ነው።

9. "ዳይሬክቶሬት" ማለት የባለሥልጣኑ የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርቡ መረጃዎችን የሚቀበልና ተያያዥ ሥራዎችን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ነው፡፡
10. "ሽልማት" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በሚቀርብ ተጨባጭ መረጃ መነሻነት የተደበቀው ግብር ሲሰበሰብ ለመረጃ አቅራቢው ተሰልቶ የሚከፈለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡
11. በዚህ መመሪያ ያልተተረጎሙ ሌሎች ቃላት ወይም ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 286/94 መሰረት መከፈል የነበረበትን የገቢ ግብር በማደብቅ፣ አሳንሶ በማያስታውቅ፣በሚያጭበረብር ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ግብር ሳይከፍል የሚቀር ግብር ከፋይን በተመለከተ በሚቀርብ ተጨባጭ መረጃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተጨባጭ መረጃ አቀራረብ፣ አመዘጋገብ፣ ይዘት እና ሽልማት

## 4. ተጨባጭ መረጃ ሊቀርብባቸው ስለሚችሉ ሁኔታዎች

ግብር የሚከፈልበትን ገቢ መደበቅ፣ አሳንሶ ማስታወቅ፣ ማጭበርበር ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ አለመክፈል ማለት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሳይወሰን የሚከተሉትን ይጨምራል ፡-

ሀ. ሆን ብሎ ገቢን መደበቅ፣
ለ. ግብር ሊከፈልበት የሚገባ ንብረትን ወይም ገንዘብን ከኢትዮጵያ ውጪ ማስወጣት፣
ሐ. ገቢን አሳንሶ ማስታወቅ፣
መ. ኪሳራ ሳያጋጥም ኪሳራ እንደደረሰ በማስመሰል የኪሳራ ሽግግር ጥያቄ ለባለስልጣኑ አቅርቦ ኪሳራው የተሸጋገረለት ከሆነ ወይም እንዲሸጋገር የተፈቀደው ኪሳራ የተጋነነ ከሆነ፣

ሠ. በህግ የተፈቀደውን ተቀናሽ ወጪ አጋኖ ማቅረብ ወይም ለግል ጥቅም የዋለ ወጪን ለንግድ ዓላማ እንደዋለ አድርጎ ማቅረብ፣

ረ. ሀሰተኛ የሆኑ ወይም በሚከፈለው ግብር ላይ ስህተት ሊያስከትሉ የሚችሉ መረጃዎችን ወይም ደረሰኞችን በመዝገብ ውስጥ ማካተት፣

ሰ. የማይገባውን ተመላሽ ከባለስልጣኑ መጠየቅ ወይም የመሳሰሉት ሁኔታዎችን ይጨምራል፡፡

## 5. የተጨባጭ መረጃ ማቅረቢያ መንገዶች

1. ማንኛውም መረጃ አቅራቢ ለዳይሬክቶሬት በግንባር፤ በፖስታ፤ በስልክ፤ በፋክስ፤በኢ-ሜል ወይም አመቺ በሆኑ በማናቸውም ሌሎች መንገዶች መረጃውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. የባለሥልጣኑ ሌሎች የስራ ክፍሎች ወይም ከባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ውጪ ያሉ ህግ አስከባሪ አካላት በአንቀፅ 4 ላይ የተገለፁትን ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ ሲደርሳቸው እንደ ነገሩ ሁኔታ መረጃ አቅራቢውን እና/ወይም መረጃውን ወደ ዳይሬክቶሬቱ በ 48 ሰዓት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 6. የተጨባጭ መረጃ ይዘት

1. የመረጃ አቅራቢው ማንነት ሚስጢራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃ አቅራቢው ዳይሬክቶሬቱ የጠየቀውን አስፈላጊ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆን ያለበት ሲሆን አንድ መረጃ ተጨባጭ ነው ለማለት የሚከተሉት መረጃዎች በአንድነት ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡

   ሀ. ግብር/ታክስ ከፋዩ የሚገኝበትን ክልል፣ከተማ ፣ክ/ከተማ፣ወረዳ፣ ልዩ ቦታ ወዘተ….፣

   ለ. የግብር/ታክስ ማጭበርበሩን ፣መደበቁን፣ በማሳነስ ማስታወቂያ ማቅረቡን ወይም በሌላ መንገድ አልከፈለም ብሎ የሚጠረጥረውን ግለሰብ/ድርጅት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ ተ.እ.ታ ቁጥር፣

ሐ. የግብር/ታክስ ማጭበርበሩ፣መደበቁ፣ በማሳነስ ማስታወቂያ መቅረቡ ወይም በሌላ መንገድ አለመከፈሉ ተፈጽሟል ብሎ የሚጠረጥርበት የግብር ዘመን እና ግብር/ታክሱ የተጭበረበረበት መንገድ፣

መ. የተጭበረበረውን፣ የተደበቀውን፣ በማሳነስ ማስታወቂያ የቀረበበትን ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ያልተከፈለውን የግብር/ታክስ ዓይነት መግለጫ፣

ሠ. መረጃ አቅራቢው ከግብር/ታክስ ከፋዩ ጋር ያለውን ወይም የነበረውን ግንኙነት፣

ረ. የመረጃ አቅራቢው ሙሉ ስም እና አድራሻ

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተቀመጠው በተጨማሪ የሚከተሉትንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ. ታክስ ከፋዩ ለማጭበርበር፣ ለመደበቅ፣ አሳንሶ ለማስታወቅ ወይም በሌላ መንገድ ላለመክፈል ጥረት አድርጓል ብሎ የሚጠረጥረውን ገቢ/ ግብር መጠን ግምት፣

ለ. በግብር/ታክስ ማጭበርበሩ ድርጊት ተካፍለዋል ብሎ የሚጠረጥራቸውን ሰዎች ብዛት፣

ሐ. በታክስ ከፋዩ ስር የሚገኙ ተቀጣሪ ሰራተኞች ብዛት ፣

መ. መረጃ አቅራቢው ከሚሰጠው መረጃ ጋር በተያያዘ ሊያቀርባቸው የሚችላቸው ሰነዶች ለምሳሌ ፡-

የደረሰኞች ኮፒ፣ሶፍት ኮፒዎች፣የግብር/ታክስ ከፋዩ ባንክ ስቴትመንት፣የባንክ ሒሳብ ቁጥር፣ የሂሳብ መግለጫ ወዘተ፣

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም በግንባር ሳይቀርብ መረጃ የሰጠ ሰው መረጃው ተቀባይነት ባገኘ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ዳይሬክቶሬቱ በግንባር በመቅረብ በንዑስ አንቀፅ 1 የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ያካተተ ዝርዝር መረጃ መስጠት አለበት፡፡

## 7. የተጨባጭ መረጃው አመዘጋገብ

1. መረጃው በግንባር ለዳይሬክቶሬቱ የቀረበ ከሆነ እና መረጃው ተጨባጭ ከሆነ በዳይሬክቶሬቱ በሚዘጋጀው በቅጽ ላይ ተሞልቶ ለመረጃ አቅራቢው አንድ ኮፒ ይሰጠዋል፡፡

2. መረጃው ለዳይሬክቶሬቱ በግንባር ያልቀረበ ከሆነ እና ተጨባጭ ከሆነ መረጃ አቅራቢው በአንቀፅ 6(3) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ መረጃውን ከሰጠ ይኸው በቅጹ ላይ ተሞልቶ ለመረጃ አቅራቢው አንድ ኮፒ ይሰጠዋል፡፡

3. የመረጃ አቅራቢዎችን ማንነት፣ አድራሻ፣ ቅጹን፣ የቀረበለትን መረጃ የሚመዘግብበት፣ የሚይዝበትንና ለሌሎች የስራ ክፍሎች የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማንዋል ዳይሬክቶሬቱ ያወጣል፡፡

## 8. መረጃው ተቀባይነት ስለሚያጣበት ሁኔታ

1. ማንኛውም መረጃ፤

ሀ. በአንቀጽ 6(1) የተመለከቱትን መረጃዎች አሟልቶ ያልቀረበ እንደሆነ ወይም ፣

ለ. የቀረበው ተጨባጭ መረጃ ቀደም ብሎ በሌላ መረጃ አቅራቢ የቀረበ ከሆነ ወይም፣

ሐ. ተጨባጭ መረጃው ከመቅረቡ በፊት ባለሥልጣኑ በራሱ የደረሰበት ወይም ተጨባጭ መረጃ የቀረበበት ግብር ከፋይ ላይ ባለሥልጣኑ ቀደም ብሎ ምርመራ ወይም ኦዲት ለማድረግ በያዘው ዝርዝር ዕቅድ ውስጥ የተካተተ ከሆነ የቀረበው መረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት ተቀባይነት የሌለው መረጃ ለዳይሬክቶሬቱ የቀረበ እንደሆነ ይህንኑ ለመረጃ አቅራቢው በ5 የስራ ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ይገልፃል፡፡

## 9. የተጨባጭ መረጃው እና የአቅራቢው ምስጢራዊነት

1. ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ ተጨባጭ መረጃ አቅራቢን ማንነት በሚስጥር ይይዛል፤ ለመረጃ አቅራቢውም የሚስጥር መለያ (ኮድ) ቁጥር ወይም ስም ይሰጣል፡፡
2. ተጨባጭ መረጃው ለሌሎች የስራ ክፍሎች በሚተላለፍበት ወቅት የመረጃ አቅራቢውን የሚስጥር ስም ወይም ቁጥር በመጠቀም ይሆናል፡፡
3. በዚህ መመሪያ መሰረት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ መረጃ በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡

## 10. ለሽልማት ብቁ ስላለመሆን

1. በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ ተጨባጭ መረጃ በሚከተሉት ሰዎች የሚቀርብ ከሆነ መረጃ አቅራቢው ለሽልማት ብቁ አይሆንም፡፡
   ሀ. በባለስልጣኑ ሰራተኞች ወይም ተሿሚዎች የቀረበ ከሆነ፣
   ለ. በፌደራል ወይም በክልል መንግስታዊ መ/ቤቶች ወይም በእነዚህ አካላት የሚሰሩ ሰራተኞች በስራ ሃላፊነታቸው ምክንያት ባገኙት መረጃ መነሻነት የቀረበ ከሆነ፣
   ሐ. ባልታወቀ ሰው የቀረበ ከሆነ፣
   መ. የግብር አለመክፈሉ ድርጊት ተካፋይ በሆነ ሰው የቀረበ ከሆነ፣
   ሠ. መረጃ አቅራቢው መረጃውን ስለማቅረቡ በአንቀጽ 7 (1) እና (2) መሰረት በባለሥልጣኑ የተሰጠውን ማስረጃ ካላቀረበ ለሽልማት ብቁ አይሆንም ፡፡

## 11. ስለሽልማት መጠን

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 ከተዘረዘሩት ውጪ ያቀረበው መረጃ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ መረጃ አቅራቢ በግብሩ ላይ የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ ተሰጥቶበት የሚፈለገው ግብር ተጠቃሎ ከተሰበሰበ በኋላ ለመረጃ አቅራቢው መረጃ ላቀረበበት የግብር ዘመን ብቻ ከተሰበሰበው ፍሬ ግብር እና ወለድ ላይ 15 በመቶ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን ሽልማት ያገኛል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ባለሥልጣኑ ከግብር ከፋዩ ጋር የግብር መክፈያ ጊዜ ስምምነት ያደረገ እንደሆነ ለመረጃ አቅራቢው ከግብር ከፋዩ ጋር በተደረገ የክፍያ ስምምነት መሰረት ከሚከፈል ግብር ላይ እየተቀነሰ ክፍያው ይፈጸምለታል፡፡
3. በሌሎች የታክስ ህጎች መሰረት የሚቀርቡ መረጃዎች በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 ለሚሰበሰበው የተደበቀ ግብር ምንጭ ከሆኑ መረጃ አቅራቢው ከተገኘው ገቢ ግብር ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የሽልማት መጠን ያገኛል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. የዳይሬክቶሬቱ ሃላፊነት

1. የቀረበለት መረጃ ተቀባይነት ያለው ከሆነ በመመሪያው አንቀፅ 6 መሰረት መዝግቦ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ያስተላልፋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

2. በቀረበው መረጃ መነሻነት የተደበቀው ግብር መሰብሰቡን ባረጋገጠ በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ የመረጃ አቅራቢውን ማንነት ሚስጥራዊነት በጠበቀ ሁኔታ በማስታወቂያ እና በሌሎች አመቺ መንገዶች (በስልክ፣ደብዳቤ ወዘተ…) ጥሪ ያደርጋል፡፡

3. ለክፍያ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን እና ተከፋይ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን በመግለጽ ለመረጃ አቅራቢው ክፍያ እንዲፈጸም ለሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋል፡፡

4. ስለተጨባጭ መረጃ አቅራቢዎች፣ በዓመት ውስጥ በቀረበው መረጃ መነሻነት የተሰበሰበውን ግብር እና ለመረጃ አቅራቢዎቹ የተሰጠውን የሽልማት መጠን እና በአጠቃላይ የስራ አፈፃፀሙን ሪፖርት ለባለስልጣኑ ያቀርባል፡፡

### 13. የሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሃላፊነት

የሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከዳይሬክቶሬቱ ለተጨባጭ መረጃ አቅራቢው የሚከፈለውን የሽልማት መጠን እና ክፍያውን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች በተላለፉለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሽልማቱን መክፈል አለበት፡፡

### 14. መብቱ የሚተላለፍ ስለመሆኑ

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጥን ሽልማት መረጃ አቅራቢው በሞት ወይም በመጥፋት ምክንያት ቀርቦ ሊቀበል ያልቻለ እንደሆነ መብቱ በህግ ለተላለፈላቸው ሰዎች ክፍያው ይፈጸማል፡፡

## 15. የመረጃ አቅራቢው ሃላፊነትና የድርጋ ድንጋጌ

1. መረጃ አቅራቢው በዳይሬክቶሬቱ ጥሪ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን ቅጽ በመያዝ ቀርቦ ክፍያውን መቀበል አለበት፡፡
2. መረጃ አቅራቢው በንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ የክፍያ ጊዜ ገደቡ ለተጨማሪ 6 ወራት ብቻ ሊራዘም ይችላል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት መረጃ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ በተመለከተው ጊዜ ቀርቦ ሽልማቱን እንዳይቀበል ያደረጉ እና መረጃ አቅራቢው ሊያስወግዳቸውም ሆነ አስቀድሞ ሊገምታቸው የማይችላቸው ሆነው መረጃ አቅራቢው እነዚህ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ሊያቀርብባቸው የሚችላቸው ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ጉዳዮች በቀድሞው መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

## 17. የተሻረ መመሪያ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 84 መሰረት ለተረጋገጠ መረጃ አቅራቢ ስለሚሰጥ ሽልማት የወጡ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ---------2003 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር